## መልመጃ አንድ፥ ተዋንያን
**Exercise One: Actors**

1. ስንት ተዋንያን ተሳትፈዋል?
2. በሴት ቡድን እና ወወንድ ቡድን በኩል የተመደቡት የሽማግሌዎች ቁጥር ስንት ነው?
3. የወንድ ቡድን ሽማግሌዎች ጥያቄ ምንድን ነው?
4. የሴት ቡድን ሽማግሌዎች ምን ዓይነት መልስ ሰጡ?
5. የሴት ቡድን አባትና እናት ምን ተመካከሩ?
6. ለትዳር/ለጋብቻ የተጠየቀችው ልጃገረድ ስሟ ማን ይባላል?
7. ለትዳር/ለጋብቻ የተጠየቀችው ልጃገረድ ስንተኛዋ ልግ ናት?
8. ትዳር የሚመሰርተው ወንድ ልጅ ስሙ ማን ይባላል?
9. የሴት ተጋቢ እናትና አባት ለምን ያህል ጊዜ ነው ቀጠሮ የሰጡት?
10. የሴት ተጋቢ ዘመድ አዝማድ የሰጡት ምላሽ አዎንታ ነው ወይስ አሉታ?

## መልመጃ ሁለት፥ምንባብ ፥ትክክለኛውን መልስ ከ ሀ፥ ለ እና ሐ ምረጡ
**Exercise Two: Reading Comprehension. Choose the right answer between A, B, and C.**

1. ቁጭ በሉ የትኛውን ይወክላል?

ሀ. አጭር የእህል መስፈሪያ ጣሳ

ለ. ረጅም የውሃ መቅጃ ጣሳ

ሐ. ተቀመጡ የሚለውን ትርጉም ነው

2. ጉዳያችንን ከሚከተሉት ለየትኛው ይስማማል?

ሀ. የመጣንበትን ምክንያት

ለ. ለምን እንደ መጣን የሚናገር ዋና ሃሳብ

ሐ. ሁለቱም

3. የተቀደሰ የሚለው __________ ን ነው::

ሀ. አግቢውን ነው

ለ. ተገቢዋን ነው

ሐ. ትዳርንና ጋብቻን ነው

4. ከእኛ የላቀ ሲል __________ ማለቱ ነው

ሀ. ከእኛ በበለጠ

ለ. ከእኛ ባነሰ

ሐ. ከእኛ እኩል

5. ትረዳላችሁ ማለት

ሀ. ትግነዘባላችሁ

ለ. ታውቃላችሁ

ሐ. ሁሉም

6. እንደ መልኩ የጠራ የሚለው ምንን ይድግፋል/ይጋራል?

ሀ. መልከ መልካምና ጠባየ ሸጋ መሆኑን

ለ. መልኩም እንደ ጠባዩ ቆንጆ መሆኑን

ሐ. ሁለቱም

7. " ግን አሁኑኑ አዎ ብለን ልንሸኛችሁ አንችልም" የሚለው ዓረፍተ ነገር ሙሉ በሙሉ ይታዎሶታል?

ሀ. አዎንታ ዓረፍተ ነገር

ለ. አሉታ ዓረፍተ ነገር

ሐ. በከፊል አዎንታና አሉታ

8. ጉዳያችሁ ላይ ተነጋግረናል÷ ጋብቻውም እንዲፈጸም ፈቅደናል፡፡ እነዚህ ዓረፍት ነገሮች ካግቢው ወገን ሲታዩ ___________ናቸው፡፡

ሀ. አስተማማኝ

ለ. አጠራጣሪ

ሐ. በእንጥልጥል ላይ ናቸው

9. ክብርና ምስጋና ሁለቱ ቃላት የሚያመለክቱት በተከታታይ __________ ነው፡፡

ሀ. የመጀመሪያው ትልቅነትን ሁለተኛው ላደረጋችሁት ድርጊት መመስግን ይገባችኋል

ለ. ትልቅነትም ተመስጋኝነትም ለሁለቱ ተጋቢዎች ብቻ ይግባል

ሐ. መልሱ አልተሰጠም

10. እጅ መንሳት______________ን ይወክላል

ሀ. ራስን ወደ ታች ማጉበጥ

ለ. ቀጥ ብሎ መቆም

ሐ. አጎንብሶ መሄድ

## መልመጃ ሦስት፦ በክፍል ሀ ያሉትን ቃላት ወይም አባባሎች ከክፍል ለ ጋር አዛምዱ

**Exercise Three: Match these words or expressions in column A with their equivalent in column B.**

| አምድ ሀ<br>Column A | አምድ ለ<br>Column B |
|---|---|
| 1. እሺ | ሀ. የቅልቅልና የስምምነት ምልክት |
| 2. ልንሸኛችሁ አንችልም | ለ. የተቀደሰ ተግባር |
| 3. ከቤተ ሰብ መነጋገር | ሐ. ቁጥርን የሚያመለክት ቅጽል |
| 4. ወዲያውኑ | መ. ድግስ |
| 5. ግብዣ | ሠ. ቁጭ በሉ |
| 6. የምግብና የመጠጥ ግብዣ | ረ. አንድን ነገር የመቀበል አዎንታዊ ቃል |
| 7. ጋብቻ | ሰ. መወያየት |
| 8. ሁለተኛ | ሸ. ከመቅጽበት |
| 9. ተቀመጡ | ቀ. በሙሉ ተስፋ ሰጥተን ማሰናበት |
| 10. መብላት መጠጣት | በ. የመግባባት ምልክት ማሳየት |

## መልመጃ አራት፦ በመዝገበ ቃላት ውስጥ ያሉትን ቃላት በመጠቀም ክፍት ቦታዎችን ሙሉ

**Exercise Four:** **Fill in the blanks by using words from the glossary**

1. ብሌን <u>ሰውነቷ ያማረ</u> ቆንጆ ናት
2. <u>ስለዚህ</u> ተብሎ ነው
3. <u>በዕውቀቱና በባህርዩ</u>
4. እንድንገልጽ፥ እንድንናገር
5. ከተለያዩ ሰዎች መካከል ፈልጎ፥ ነቅሶ ኃላፊነት መስጠት
6. የበለጠ ነገሩን ታውቃላችሁ
7. ጠባየ ሸጋና ጠባየ መልካምም ለሆነ ሰው ሽምግልና መመረጥ ክብር ይሆናል
8. በእድሜ መቆየት ወይም ረጋ ብሎ የበሰለ ሃሳብ በመስጠት የሚታወቅ የቆይታ ወቅት _______________ ይባላል፡፡
9. ከፍተኛ ንቃተ ህሊናን ተመርኩዞ ለሰዎች የሚጥም ተግባራትን የማከናወን ችሎታ _______________ ተብሎ ይጠራል፡፡
10. በጉዳያችሁ ላይ ተነጋግረን፥ ተስማምተን ጨርሰናል፡፡

## መልመጃ አምስት፥ የተሰመሩትን ቃላት በተመለከተ ጥያቄዎች ጠይቁ

**Exercise Five: Ask questions corresponding to the underlined words**

1. ጤና ይስጥልኝ
2. ይፈቀድልን
3. ዓለም
4. የላቀ
5. ልጆች ይወለዳሉ
6. ክብር
7. መተዳደሪያ
8. መመካከር
9. ይቀጠራል
10. በትህትና እንጠይቃለን

## መልመጃ ስድስት፥የማዳመጥ ምንባብ፥ ውይይቱን ተመልከቱና በእያንዳንዱ መሥመር ላይ ያላችሁን አስተያየት ስጡ።

**Exercise Six: Listening comprehension. Watch the conversation and comment each line**

1. የወንድ ቡድን ተጠሪ - አንቀመጥም። የመጣንበትን ጉዳይ አስረድተን መልሱን ሳናገኝ ፥ ጉዳያችንን ቆመን እንድናስረዳ ይፈቀድልን።

2. የወንድ ቡድን ተጠሪ - የመጣንበት ጉዳይ እጅግ ከፍተኛ ስለሆነ፥ ክብደት ያለው ስለሆነ ቆመን እንድናስረዳ ይፈቀድልን።

3. የወንድ ቡድን - መቼም በዚህ ዓለም ልጆች ይወለዳሉ፥ ያድጋሉ፥ ለቁም ነገርም ሲደርሱም... በትህትና እንጠይቃለን።

4. የሴት ቡድን - መልካም! ጥያቄያችሁ ተገቢም የተለመደም ነው።

5. የወንድ ወገን - እሺ! እግዜር ያክብርልን! ቀጠሮውን ቀን እንድትቆርጡልን በትህትና እንጠይቃለን። አባትና እናት በመመካከር የዛሬ ሳምንት እሁድ በአምስት ሰዓት አካባቢ ሊመጡ ይችላሉ።

6. “ ለዚህ ቀን ቀጠሮ ሰጥታችሁን በደስታ ተመልሰን ሄደናል፥ ዛሬ የመጣነው ደግሞ መልስ ለመስማት ነው።”

7. የሴት ቡድን - ጉዳያችሁ ላይ ተነጋግረናል።ጋብቻውም እንዲፈጸም ፈቅደናል

8. የወንድ ቡድን - “በጣም እናመሰግናለን ለሰጣችሁን አክብሮት ክብርና ምስጋና ለእናንተ ይሁን።” ክብርና ምስጋና ለማን ነው?

9. የሴት ቡድን - ቁጭ በሉ፥ ተቀመጡ። ለምን ግለጹ

10. የወንድ ቡድን - እንግዲህ ሁለቱ ተጋቢዎች ከቤተሰቦቻቸው ጋር ተነጋግረው የጋብቻውን ቀን እንዲወስኑ ፈቃዳችሁን እንጠይቃለን። የተጋቢዎቹን ስም ለይታችሁ አስቀምጡ

## መልመጃ ሰባት፥ አዎንታ ወይም አሉታ ጥያቄዎች

**Exercise Seven: yes or no questions**

| | አዎን | አይደለም |
|---|---|---|
| 1. የወንድ ቡድን የሴቶች የወካዮች ናቸው | | |
| 2. የሴቶች ተወካዮች ሴቶችን ይወክላሉ | | |
| 3. ተጋቢዎች ስንል ወንድና ሴትን ነው | | |
| 4. ጤና ይስጥልኝ ከሰላምታ አለዋወጥ አንዱ መንገድ ነው | | |
| 5. በገጠር ብዙ ዘመናዊ ጋብቻዎች ይካሄዳሉ | | |
| 6. በአዲስ አበባ ከተማ ባህላዊ ጋብቻዎች ይታያሉ | | |
| 7. በኢትዮጵያ ባህል አዋቂዎችን ስናገኝ ከወንበራችን እንነሳለን | | |
| 8. እግዜር ያክብርልን ሲሉ ሽማግሌዎቹን መስደብ ነው | | |
| 9. ትዳርና ጋብቻ የተቀራረበ ትርጉም ያላቸው ቃላት ናቸው | | |
| 10. መቀላቀል ማለት መዛመድ ማለት ነውፀ | | |

## መልመጃ ስምንት፥ ተቃራኒ የሆኑትን ቃላት በመልመጃው ውስጥ ፈልጉ

**Exercise Eight: Find the antonyms of these words in the text.**

1. ሃሳብ መለዋወጥ
2. ከፍተኛ ጉዳይ
3. ክብደት ያለው ጉዳይ
4. ለቁም ነገር መድረስ
5. የተቀደሰ ተግባር
6. መልክ የጠራ
7. በትህትና መጠየቅ
8. የላቀ
9. አዎንታ
10. ዘመድ አዝማድ

## መልመጃ ዘጠኝ፥ ውይይቱን በራሳችሁ አባባል/ቃላት አሳጥራችሁ ጻፉ

**Exercise Nine: Summarize the dialogue in your own words.**

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

____________________________________________________________________________

## መልመጃ አስር፥ ኪነት መሥራት፡፡ ኪነቱን ተለማምዳችሁ የከተማውን አማርኛ በመጠቀም ዝግጅት አቅርቡ፡፡ ይህ ዝግጅት ባህሉን፥ አቀረራረቡን እና ሌሎች የቋንቋው ስልቶች እንዲገቡ ያስፈልጋል፡፡

**Exercise Ten: Role play:** Rehearse and perform the skit by using urban Amharic. Be mindful to reflect the local culture, gestures and other kinesics aspects of language